

# የጴጥሮስ ራዕይ

ቆርኔሌዎስ ቂሳርያ ተብላ በምትጠራ ከተማ የሚኖር ሮማዊ ወታደር ነበር። ከበታቹ መቶ ወታደሮችን የሚመራ የመቶ አለቃ ነበር። እርሱና መላ ቤተሰቦቹ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ነበሩ። ድሆችን ይረዱና ያለመቋረጥም በእግዚአብሔር ፊት ይፀልዩ ነበር።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ቆርኔሌዎስ ራዕይን አየ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በዚህ መልኩ ይገናኛል። ቆርኔሌዎስም በዚህ ራዕይ የተመለከተው መልአክን ነበር። መልአኩም፣ "ቆርኔሌዎስ ሆይ፣" ብሎ ጠራው።

ቆርኔሌዎስም ይህ ራዕይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ አውቆ እጅግ ፈራ። "ጌታዬ፣ ምንድነው?" ብሎ ጠየቀ።

መልአኩም ቆርኔሌዎስ ለድሆች ሲያደርግ የነበረውን በጎነት እንዳየና ፀሎቱ በሙሉ እንደተሰማ ነገረው።

ኢዮጴ ወደሚባለው ከተማ ሰዎችን እንዲልክና በባሕር ዳርቻ በሚገኘው በቁርበት ፋቂው በስምኦን ቤት በእንግድነት ያረፈውን ጴጥሮስን እንዲያስመጣ አዘዘው።

መልአኩ ከሄደ በኋላም ቆርኔሌዎስ ሁለቱን አገልጋዮቹን ከአንድ ከሚያምነው ወታደሩ ጋር ወደ ኢዮጴ ሄደው ጴጥሮስን ይዘውት እንዲመጡ አዘዛቸው። ኢዮጴ ከቂሳርያ ወደ 48 ኪሎ ሜትር ያህል የምትርቅ ከተማ ነበረች።

በዚያን ጊዜ አይሁዳዊ ያልሆኑ ሰዎች "አሕዛብ" በመባል ይታወቃሉ። በአይሁዳውያን ዘንድም ተቀባይነት ያልነበራቸውና እጅግ የተናቁ ሰዎች ነበሩ። ምክንያቱም እንደአይሁዳውያን "በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች" ስላልሆኑ ነበር። አይሁዳውያን ከአሕዛብ ጋር አይተባበሩም፤ ምንም አይነት ስምምነትም አያደርጉም ነበር።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የሆነው ቆርኔሌዎስ አይሁዳዊ ወደሆነው ወደ ጴጥሮስ ወደቤቱ እንዲመጣ ሲልክበት እንመለከታለን። የጴጥሮስ ምላሽ ምን ይሆን? በሕጉ መሠረት ካልነፃ ሰው ጋር ምንም አይነት ሕብረት ሊኖረው አይገባም ።

በሚቀጥለው ቀን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በሚሆንበት ጊዜ ሶስቱ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ወደኢዮጴ ከተማ እየተጓረሱ ነበር። ጴጥሮስ ደግሞ ምግብ እስከሚበስል ድረስ ተርቦ ነበር። ምግብ እስከሚቀርብም በጣራው ላይ ይፀልይ ነበር። የዚያን ዘመን ጣሪያዎች ለጥ ያሉ ነበሩ። ሞቃት በሚሆንበት ወቅት የቤተሰቡ አባላት በጣሪያው ላይ ይተኛሉ። የሙሴ ሕግ ሰዎች ቤት በሚሰሩበት ወቅት በጣሪያው ዙሪያ ሰው እንዳይወድቅ መከላከያ የሚሆን ግድግዳ በጣሪያው ጠርዝ ዙሪያ ሊሰሩ እንደሚገባ ይገልፃል። (ዘዳግም 22፡8) የግድግዳው ርዝመትም ወደ አራት ጫማ ከፍታ ነበረው።

ታዲያ ጴጥሮስ እየፀለየ እያለ እንቅልፍ ተጫጫነው። ሕልምን ማለምም ጀመር። በሚያየው ሕልምም ሰማይ ተከፍቶ አንድ ትልቅ አንሶላ በአራት ጠርዞቹ ተይዞ ሲወርድ ይመለከታል። በዚህ አንሶላ ላይም ሁሉም አይነት አራት እግር ያላቸው እንስሳት፣ አእዋፍና በምድር ላይ የሚሳቡ እንስሳት ነበሩበት።

ከዚያም አንድ ድምፅ፣ “ጴጥሮስ ተነሳ፣ አርደህ ብላ፣” ብሎ አዘዘው። በሙሴ ሕግ መሠረት አንዳንድ እንስሳት ንፁሕ ናቸው። ስለዚህም ይበላሉ። አንዳንድ እንስሳት ግን ያልነፁ ስለሆኑ አይበሉም። እስራኤላውያን ያልነፁ እንስሳትን እንዲበሉ የሙሴ ሕግ ይከለክላቸው ነበር።

የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትን ዝርዝር በሌዋውያን ምዕራፍ 11 ውስጥ ማንበብ ይቻላል። ያልነፁ እንስሳት ከሚባሉት ውስጥ ግመል፣ ጥንቸል፣ እንሽላሊት፣ አሳማና ሽኮኮ ይገኙበታል። የአሳማ ስጋን በምንም አይነት መልኩ መብላት አልተፈቀደላቸውም። ቅርፊትና ክንፍ የሌላቸውን የአሳ ዝርያዎችም አይበሉም። ከአእዋፍ ዝርያዎችም እንደጥንብ አንሳ፣ ንስር፣ ጭልፊት፣ የሌሊት ወፍ፣ ገዲ፣ቁራ የመሳሰሉትን እንዲበሉ አልተፈቀደላቸውም።

ታዲያ ጴጥሮስ ምን ያደርግ ይሆን? ያልነፃ እንስሳ እንዲበላ አልተፈቀደለትም። ደግሞ የሰማው ድምፅ፣ “እረድና ብላ፣” ብሎ አዞታል።

ጴጥሮስም ለዚያ ለሰማው ድምፅ ምላሽ ሲሰጥ፣ “ጌታ ሆይ፣ በሕይወት ዘመኔ ያልነፃ ነገር ከቶ በልቼ አላውቅም፣” አለ።

ያ ድምፅም ለሁለተኛ ጊዜ ተናገረው። እንዲህም አለው፣ “እግዚአብሔር ንፁሕ ነው ያለውን አንተ ርኩስ ነው ብለህ ልትጠራ አትችልም።”

ለሶስተኛ ጊዜም፣ “አርደህ ብላ፣” ካለው በኋላ አንሶላው እንደገና ወደሰማይ ተወሰደ።

የራዕዩ ትርጉም ምን እንደሆነ እያሰበ ሳለም ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሶስት ሰዎች መጡ። በበሩ ላይ ቆመውም ስምኦን ጴጥሮስን እንዲጠራላቸው ጠየቁ። እግዚአብሔር አስቀድሞ ጴጥሮስን አዘጋጅቶት ነበር። የእግዚአብሔር መንፈስም ጴጥሮስን ሶስት ሰዎች እየፈለጉት እንደነበር ነገረው። ከእነርሱም ጋር መጓዝ እንዳለበት አስገነዘበው። ሰዎቹንም ወደእርሱ የላካቸው መንፈስ ቅዱስ እርሱ ራሱ እንደሆነም ነገረው።

ጴጥሮስም መንፈስ ቅዱስን ታዞ ወደታችኛው ክፍል ወርዶ የሚፈልጉት እርሱን እንደሆነ ገለጠላቸው።

“ለምንድነው የመጣችሁት?” ብሎም ጠየቃቸው። እነርሱም ለጌታቸው መልአክ ተገልጦለት ወደኢዮጴ ሰዎችን ልኮ ጴጥሮስን እንዲያስመጣ እንዳዘዘው ነገሩት። ከዚያም ወደቤት ውስጥ እንዲገቡ ከጋበዛቸው በኋላ አስተናገዳቸው።

ታዲያ ጴጥሮስ ከዚህ በኋላ አሕዛብን “ያልነፁ” ብሎ መጥራት እንደሌለበት ተገነዘበ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ተቀብሏቸዋልና። እግዚአብሔር ከተቀበላቸው ደግሞ ጴጥሮስም የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም ዜና የመናገር ኃላፊነት ነበረበት።

ጴጥሮስ በቂሳሪያ ያጋጠመው ምን እንደነበር ለማወቅ ትችሉ ዘንድ የሚቀጥለውን ታሪክ አንብቡ።

*የጴጥሮስ ራዕይ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 10፡ 1 – 23 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com